## ሳምንታዊ ዜና ዘገባ

**ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ራዲዮ ጥር 16 ቀን 2001 ዓ.ም.**

- ወያኔ በፈጠረዉ ችግር ምክንያት የሃይማኖት ግጭ በአዲስ አበባ ከተማ ሊቀሰቀስ እንደነበረ ተጋለጠ፣

- በወያኔ የነፍስ አባት ተጠርቶ የነበረዉ የመስቀል አደባባዩ ሰላማዊ ሰልፍ ከፀጥታ ጋር በተያያዘ ላልተወሰነ ጊዜ ተራዘመ፣ በርካታ ወጣቶች ከቤተክርስቲያንና ከመስጊድ እየታፈሱ ወዳልታወቀ ስፍራ ተወሰዱ፣

- ወያኔ በድብቅ ስናይፐር የታጠቀ አንድ ብርጌድ ጦር አዲስ አበባ ማስገባቱ ታወቀ፣

- ለሽምግልና በመለሰ ዜናዊ ትዕዛዝ የተላኩት አዛዉንት ዛቻና ስድብ ደረሰባቸዉ፣

- ቄስ ኢተፋ ጎበና ቅስናቸዉ ተገፈፈ ከስልጣናቸዉም ተነሱ፣ የወያኔ ብሄራዊ መረጃና ደህንነት ቢሮ ያቀነባበረዉ ሀሰተኛ ሰነድ እንደነበረ ተጋለጠ፣

- ሁለት የወያኔ ባለስልጣናት ከስልጣናቸዉ ተባረሩ የሚሉና ሌሎችም ይገኙበታል።

**ዝርዝሩን ከሚቀጥለዉ ገጽ ጀምረዉ ያንብቡ <<<>>**

የወያኔ ቡድን በፈጠረው መሰሪ ስራ ምክንያት በሀገሪቱ ውስጥ ከፍተኛ የሀይማኖት ግጭት ሊቀሰቀስ እንደነበር ከደረሰን ዘገባ ለመረዳት ተችሎዋል::

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ወያኔ የተበላሸበትን እና የወደቀበትን ፖለቲካውን ለማንሳት በማሰብ ተቻችሎና ተፋቅሮ የኖረውን የኢትዮጵያ ህዝብ በሀይማኖት ከፋፍሎ እልቂት እንዲፈጠር እና ብጥብጥ እንዲነሳ ውስጥ ውስጡን በደህንነት ሰራተኞቹ አማካኝነት ከፍተኛ ስራ ሲሰራ የከረመ ቢሆንም በአርቆ አስተዋይ የሀገሪቱ ህዝቦች ሙከራው የከሸፈ መሆኑንና ጥቂት የወያኔ ተልዕኮ የተሰጣቸው ጥቅመኛ ግለሰቦች ግን አሁንም ውስጥ ውስጡን አስጊ እንቅስቃሴ እያደረጉ ናቸው::

ዘረኛ እና ጎጠኛው የወያኔ ቡድን የሚያራምደው የፖለቲካ እንቅስቃሴ ምንም ያልተሳካለት መሆኑን ሲያረጋግጥ በኢትዮጵያ ህዝብ መሀል ገብቶ በሀይማኖት ምክንያት እርስ በርስ እንዲበጣበጥ ከዚህ ቀደም በተደጋጋሚ ሙከራ አድርጎ ሳይሳካለት የቀረ ቢሆንም በቅርቡ ግን ጥቂት የእምነት አባት ነን ባሉ ለግል ጥቅማቸው እንጂ ለህዝብና ለሀይማኖታቸው ቀናኢ ባልሆኑ ሰዎች አማካኝነት በህዝቡ መሀከል ብጥብጥና እልቂት እንዲፈጠር ሲሰሩ እንደነበርና ድርጊታቸውም እንደተጋለጠ የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል::

ሰሞኑን በየቤተክርስቲያኑና በየመስጊዱ ግቢ ውስጥ በወያኔ በተመለመሉ ሰባኪ ነን ባይ የእምነት ጭምብል ባጠለቁ አስመሳይ የወያኔ ካድሬ የደህንነት ሰዎች አማካኝነት እየተዘዋወሩ ህዝብን ለእልቂት የሚጋብዝ ቅስቀሳ ሲያደርጉ የሰነበቱ ሲሆን በሁለቱም ሀይማኖት ሰባኪዎች የተጀመረው ሰንካላ ቅስቀሳ በህዝቡ አርቆ አስተዋይነት ችግር ሳይፈጠር መቅረቱ ታውቆዋል::

ህዝቡ የወያኔን ከንቱ ቅስቀሳ እና ያልረባ ሙከራ ወደ ጎን ትቶ በወያኔ ላይ በማነጣጠሩ የተደናገጠው ይኸው መሰሪ ቡድን ጨኸቷን ቀሙኝ እንዲሉ በስውር የጀመረው አፍራሽና ህዝብ ጨራሽ ተልእኮው አልሳካ ሲለው መልሶ ለህዝቡ ተቆርቋሪና ሀይማኖት ጠባቂ ብሎም ለህዝብ ሰላም መከበር የቆመ መስሎ እንደገና ሰሞኑን የማስጠንቀቂያ አዋጅ ማወጁ ታውቆዋል::

ረቡዕ ጥር 13 ቀን 2001 ዓ. ም. የወያኔ የፌዴራል ፖሊስ በወጣው በዚሁ አዋጅ ላይ እንደገለፀው ከሆነ « በአሁኑ ሰዓት በሀገሪቱ በተለይም በመዲናይቱ እየታየ ያለው አላስፈላጊ የሀይማኖት ቅስቀሳ ወዳልተፈለገ አቅጣጫ ሊያመራ ስለሚችል ይህንን ለማስከበር የኃይል እርምጃ ለመውስድ እገደዳለሁ» በማለት እንዳያማህ ጥራው እንዳይበላ ግፋው እንዲሉ መግለጫ መስጠቱ ታውቆዋል::ቀድሞም በህዝቡ መሀል የነበረውን የሀይማኖት እኩልነት ንዶ ለራሱ ፖለቲካ መጠቀሚያ ለማድረግ ከላይ እታች ሲዋትት ቢኖርም በህዝቡ ቆራጥ እርምጃ አልሳካ ያለው ወያኔ መልሶ ለህዝብና

ለወገን ተቆርቆዋሪ መስሎ መግለጫ ማውጣቱ አስገራሚ ነው ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ገልፀዋል፡፡

እነ አባ ገ/መድህን በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የጥምቀት በዓልን ተንተርሶ በካኒተራ መልክ አሳትሞ ባሰራጨው መልእክት ከክርስትና ውጭ በኢትዮጵያ ውስጥ ምንም አይነት እምነት እንደሌለ አስመስሎ ተፋቅሮ ከኖረው ሙስሊም ወገኑ ጋር ለማጋጨት እና እልቂት እንዲፈጠር አስቦ የነበረ ቢሆንም ህዝቡ ባለው ትዕግስትና አርቆ አስተዋይነት ችግሩ ሳይፈጠር የቀረ ከመሆኑም በላይ ይባስ ብሎ በበዓሉ ላይ የተገኘው ህዝበ ክርስቲያን በአባ ገብረ መድህን ድርጊት ቁጣውን ሲገልጽ በፌዴራል ፖሊስ እርዳታ ከአካባቢው ሊሰወር እንደቻለ ከደረሰን ዘገባ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

የወያኔ ሹመኛ ካድሬ የሆነው ሼህ ኤልያስ ሬድዋን የተባለው ግለሰብ በበኩሉ የኢትዮጵያን ህዝብ አኑዋኑዋርና ባህል ባልጠበቀ ብሎም የሀይማኖት እኩልነትን በናደ መልኩ የሚገልጽ በራሪ ወረቀቶችን አባዝቶ በመስጊድና በመርካቶ አካባቢ ያስበተነ እና ሙስሊሙ በክርስቲያን ወንድሙ ላይ እንዲነሳና እልቂት እንዲፈጠር ሙከራ ያደረገ ቢሆንም በየመስጊዱ ባሉ የእምነት አባቶችና የእድሜ ባለፀጋዎች ያለምንም ችግር በሰላም ሊከሽፍ እንደቻለ የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል፡፡

ያሰበው ሁሉ ያልተሳካለት የወያኔ ቡድን ከሰሞኑ በየቤተክርስቲያኑ እና በየመስጊዱ ውስጥ በጸሎት ላይ የነበሩ ወጣቶችን እያፈሰ ወዳልታወቀ ስፍራ እያጉዋጉዋዘ ሲሆን እስከ ትናንትና ድረስ የታፈሱ ወጣት ቤተሰቦች ልጆቻቸው የት እንዳሉ አለማወቃቸውን ከደረሰን ዘገባ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

ወያኔ በህዝቡ መሀል ክፍተት እንዲፈጠር ሲቆፍርና ሲሰረስር የነበረው መሰሪ ሴራ አልሳካ ሲለው እራሱ ያመጣውን ችግር ለህዝብና ለሀገር ደህንነትና ሰላም አሳቢ መስሎ ጸሎት ሊያደርጉ ቤተክርስቲያንና በመስጊድ ውስጥ የገቡ ወጣቶችን እያፈሰ ወዳልታወቀ ስፍራ እያጋዘ መሆኑን ያጋለጠው ዘገባ የሁለቱም የሀይማኖት ተከታዮች የወያኔን መሰሪ አካሄድ ጠንቅቀው አውቀው ሊያመክኑትና ቀድሞ እንደነበረው ፍቅርና መተሳሰብ ሊቀጥሉ እንደሚገባም የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ የሁለቱም እምነት ተከታይ የሆኑ የእድሜ ባለፀጋዎች ጥሪ አስተላልፈዋል፡፡

የሰሩት መሰሪ ስራ ውጤት አልባ ከመሆኑም ባሻገር በህዝቡ ዝምታ የተደናገጠው መለስ የፌዴራል ፖሊስ ከፍተኛ መኮንኖችን፤ የመከላከያ ኤታማጆር ሹም የሆነውን ጄ/ል ሳሞራ የኑስንና የደህንነት ከፍተኛ ባለስልጣናትን ረቡዕ ጥር 13 ቀን 2001 ዓ. ም. በቤተ መንግስት አስጠርቶ ከፍተኛ አጣብቂኝ ውስጥ እንደገቡና ከ1997 ዓመተ ምህረቱ በበለጠ ተቃውሞና ችግር ሊፈጠርባቸው ስለሚችል ሁሉም ጦር በተጠንቀቅ እንዲቆምና የህዝብ እንቅስቃሴ ቢጀመር ነፃ እርምጃ እንዲወስዱ ትዕዛዝ መስጠቱን ከቤተ መንግስት ምንጮች የተገኘው ዘገባ አስረድቶዋል፡፡

በዚህም ምክንያት ሜ/ጀ/ል ሰዩም ሀጎስ ከሚመራው ከምዕራብ እዝ ስናይፐር የታጠቀ አንድ ብርጌድ ጦር ባስቸኩዋይ በአንድ ሌሊት አዲስ አበባ ከተማ ገብቶ እንዲመሽግ መለስ በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት በስውር እና በድብቅ ገብቶ የመሸገ ሲሆን በድብቅ ሰልጥነው ሁርሶ ተቀምጠው የነበሩ ቁጥራቸው ከ5 ሺህ በላይ የፌዴራል ፖሊሶች ፈጥነው እንዲገቡ በታዘዘው መሰረት ምሽቱን ተጉዋጉዘው አዲስ አበባ ከተማ መግባታቸውን የቤተ መንግስት ምንጮች አጋልጠዋል፡፡

በወያኔ የነፍስ አባት በአባ ገ/መድህን ተጠርቶ የነበረው የመስቀል አደባባይ ሰላማዊ ሰልፍ በብሄራዊ መረጃና ደህንነት ቢሮ መታገዱ ተገለፀ፡፡ ከ6 ወር በፊት ዕቅድ ተይዞለት የነበረው ይኸው ሰላማዊ ሰልፍ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሀገሪቱ በተከሰቱት የሀይማኖት ግጭት ስጋቶች ጋር በተያያዘ በአሁን ወቅት ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ አስቸጋሪ ስለሆነ ለሌላ ጊዜ እንዲተላለፍ የብሄራዊ መረጃና ደህንነት ቢሮ በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት አባ ገ/መድህንም ላልተወሰነ ጊዜ እንደተራዘመ በመገናኛ ብዙሀን አስታወቀዋል፡፡

ለብዙ ዓመታት የመካነ ኢየሱስ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን ፕሬዝዳንት የነበሩት ቄስ ኢተፋ ጎበና በፖለቲካ እና በሙስና ሰበብ ቅስናቸው ተገፍፎ ከስልጣናቸው መባረራቸውን የደረሰን ዘገባ ገለፀ፡፡

ቄስ ኢተፋ ጎበና በቅርቡ ከኦነግ ጋር እንዲያደራድሩዋቸው በወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ተመርጠው የሽማግሌዎቹ ሰብሳቢ ሆነው በደብዳቤና በቃል ትዕዛዝ ተሰጥቶዋቸው ሽምግልናውን የሞከሩ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ ተጠልፈው ለዚህ ችግር ሊዳረጉ እንደቻሉ የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል፡፡

የአማራ ብሔር ተወላጅ የሆኑትን የልጆቻቸውን እናት በማግባታቸው በዚያው ቤተክርስቲያን ባለስልጣናት እና በጉዋደኞቻቸው ከዚህ ቀደም ብዙ ፈተናዎች እና ችግር አጋጥሞዋቸው እንደነበረ ያስታወሰው ዘገባ አሁን ደግሞ እነ መለስ ዜናዊ እራሳቸው ሾመው ሽምግልናው አልሳካ ሲላቸው መልሰው ጠልፈው ከስልጣናቸው እንዲባረሩ ማድረጋቸው ታውቆዋል ሲል ዘገባው አስረድቶዋል፡፡

ቄስ ኢተፋ ጎበና በቅርቡ ግን ኦነግን አሸማግሉን ብሎ የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ በደብዳቤ ጭምር ትዕዛዝ የሰጣቸው ከመሆኑ ጋር በተያያዘ የተጉዋዙበት ሽምግልና ውጤት ባለማግኘቱና ይህንኑ ሁኔታ በመገናኛ ብዙሀን ይፋ በማውጣታቸው በነመለስ ጥርስ ተነክሶባቸው ቆይቶ ሰሞኑን ከስልጣናቸው ተባርረው ቅስናቸውም እንዲገፈፍ መደረጉን ይኸው የደረሰን ዘገባ አብራርቶዋል፡፡

ወያኔ ከኦነግ መሪዎች ጋር እንዲያደራድሩት እና እንዲያሸማግሉት የሽማግሌዎቹ ሰብሳቢ አድርጎ ሾሞዋቸው ከአንድም ሁለት ጊዜ ወደ ውጭ ሀገር በመመላለስ በሽምግልናው ጥረት ቢያደርጉም እንዳልተሳካላቸውና ይህም እነመለስን ያላስደሰተና ያስከፋ መሆኑን የገለፀው የደረሰን ዘገባ «ከኦነግ ጋር ስትሞዳሞዱ ከረማችሁ እንጂ መቼ ለማስታረቅ ሄዳችሁ» በሚል ከመለስ ዜናዊ ቁጣና ተግሳፅ እንደደረሰባቸው ለመረዳት ተችሎዋል።

ይህ በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳለ መለስ ዜናዊ በተወካዮች ምክር ቤት ተብየው ውስጥ የተቃዋሚ የምክር ቤት አባሎች ከኦነግ ጋር ድርድር ማድረጋችሁ ይሰማል በዚህ ዙሪያ ላይ ማብራሪያ ይሰጠን ብለው ጥያቄ ያቀረቡ ሲሆን ሁሌም አይኔን ግንባር ያድርገው ማለት የሚወደው መለስ ዜናዊ « ከኦነግ ጋር ድርድር አልተደረገም፤ሊደረግም አይችልም » በማለት ምላሽ በሰጠ በጥቂት ቀናት ውስጥ ቄስ ኢተፋ ጎበና የተላኩበትን ሽምግልና ውጤት በቲሌቪዥንና በሬዲዮ ከኦነግ ጋር ድርድሩ እንደተደረገ ነገር ግን ውጤት እንዳላስገኘ በይፋ በመግለፃቸው በቤተክርስቲያኑዋ ውስጥ ባሉ አጎብዳጅ ቄስ መሳይ ካድሬዎች በኩል ተንኮልና ሸር ሲውጠነጠን ቆይቶ ዛሬ ስልጣናቸውንና ቅስናቸውን ሊነጠቁ እንደበቁ ምንጮቹ አጋልጠዋል።

ለዚህም ስራ ተባባሪ እና ተሳታፊ ይሆናሉ የተባሉ የመካነ ኢየሱስ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን ውስጥ የሚሰሩ ጥቂት ጥቅመኞችን በዚሁ ተንኮል ስራ ላይ አሰማርቶ በተለይ በብሄራዊ መረጃ እና ደህንነት ክፍል በሚባለው የወያኔ ቡድን ሀሰተኛ ሰነዶች ተቀነባብረው እንዲዘጋጁ ተደርጎ በቤተክርስቲያን ደረጃ ጉዳዩ እንዲያዝ እና አጣሪ ኮሚቴ እንዲዋቀር አድርገው ድራማውን በ15 ቀናት ውስጥ አቀነባብረው ሰርተው የጨረሱ መሆኑን የገለፀው ደረሰን ዘገባ በቀጣይነትም ምናልባት ከሙስና ወይም ከፖለቲካ ጋር አያይዘው ወደ ዘብጥያ ሊያወርዱዋቸው እንደሚችል ዘገባው ስጋቱን ገልፆዋል።

በተለይ በወያኔ መረጃና ደህንነት ቡድን ተዘጋጅቶ አጣሪ ኮሚቴ ለተባለው የቀረበው ምስጢራዊ ሰነድ እንደሚለው ከሆነ «ቄስ ኢተፋ ጎበና የእምነት አባት መሆናቸው እየታወቀ ፖለቲካ ውስጥ ተዘፍቀው መገኘታቸው የቤተክርስቲያንዋን ስም የሚያጎድፍ ከመሆኑም በተጨማሪ በእምነቱ ተከታዮች ላይ ከፍተኛ ክትትል እንዲደረግ የሚያስችል ድርጊት ሲፈጽሙ ተገኝተዋል» የሚል እንደሚገኝበትም የደረሰን ዘገባ አብራርቶዋል።

በወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ትዕዛዝ ለሽምግልና የተላኩት ቄስ ኢተፋ ጎበና ላይ በስውር በነመለስ በተሰጠ ትዕዛዝ በተቀነባበረ ዘዴ እንዲጣራ ተብሎ ውሳኔ እንዲሰጥ ተደርጎ ቅስናቸው እንዲገፈፍ እና ከፕሬዝዳንትነታቸው እንዲነሱ በመደረጉ በርካታ የእምነቱ ተከታዮች እንደተከፉና እንዳዘኑ ይሄው የደረሰን ዘገባ ጨምሮ ገልፆዋል።

አንቺው ታመጪው አንቺው ታሮጪው እንዲሉ ወያኔ እራሱ አሸማግሉኝ ብሎ ውጤቱ ሳይሳካ ሲቀር « ከኦነግ አመራሮች ጋር ስትሞዳሞዱ ነበር» ብሎ ሰበብ ፈልጎ ይህን የመሰለ እርምጃ መውሰዱ አሳፋሪና አሳዛኝ ወያኔ ያለበትን ውስጣዊ ችግርና ፍርሀት አጉልቶ የሚያሳይ ነው ሲልም ዘገባው አስረድቶዋል።

ለብዙ ዓመታት ከበረሀ ጀምሮ አብሮ የመጣው ቀንደኛው ወያኔ ስብሀት ነጋ ስራውን በብቃት መወጣት አልቻለም በሚል ሰበብ ከኤፈርት ዋና ስራ አስኪያጅነቱና ከማዕከላዊ ኮሚቲ አባልነቱ የተሰናበተ መሆኑንና በሌሎችም ላይ እንደሚቀጥል ይኸው የደረሰን ዘገባ ያስረዳል።

አሁን የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ የሆነው የኩማ ደመቅሳ አስተዳደር ባለስልጣናቱን እያባረረ በሙስና ሰበብ ወደ ዘብጥያ እየከተታቸው እንደሚገኝ ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሎዋል።

የ10 ክፍለ ከተሞች የመሬት አስተዳደር ኃላፊዎችን ከወራት በፊት ያባረረና አንዳንዶቹን በሙስና ሰበብ እስር ቤት የከተታቸው ሲሆን ሰሞኑን ደግሞ ሁለት ከፍተኛ የመምሪያ ኃላፊዎች ከስልጣናቸው እንዳባረራቸው ከደረሰን ዘገባ ለመረዳት ተችሎዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ፅዳት ውበትና ልማት ኤጀንሲ ዋና ስራ አስኪያጅ አቶ ሙሳ ሀሰን እና ምክትል ስራ አስኪያጁ አቶ ሙሉጌታ ቢሰውር የተባሉት የወያኔ ካድሬዎችን ስራን በአግባቡ አለመወጣት በሚል ከስልጣናቸው ያባረራቸው መሆኑ ታውቆዋል።

አቶ ሙሳ ሀሰንና አቶ ሙሉጌታ ቢሰውር የተባሉት ሁለቱ የወያኔ ካድሬ ባለስልጣናት የአዲስ አበባ ከተማ ፅዳትና ውበት እንዲሁም ልማት የሚቆጣጠሩ የነበረ ሲሆን በዓመት ከ100 ሚሊዮን ብር በላይ በጀት ተመድቦለት የሚንቀሳቀሰውን ቢሮ ሲያንቀሳቅሱ እንደነበርና ሰሞኑን በተደረገ ግምገማ ከስልጣናቸው መባረራቸውን የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል።